# የኢትዮጵያ የዘመን ቀመር

ዮሐንስ እሸቱ
የቅኔ የብሉያት ትርጓሜና
የአቡሻኽር መምህር

# የዘመን ቀመር (Calendar System)

## The Balinese Pawukon Calendar

One of two calendars used on the Indonesian island of Bali, the Pawukon calendar year is two hundred and ten days long and consists of six thirty-five-day months, a number which reflects the ancient rice-growing cycles of the island.

# የዘመን ቀመር (Calendar System)

## The Chinese Calendar

Although modern-day China relies on the Gregorian calendar, the traditional Chinese calendar still governs the dates of important holidays such as the Chinese Lantern Festival, and it is also used as a tool for selecting auspicious dates for weddings, funerals, moving, and starting businesses. The Chinese calendar is essentially a lunar calendar, with twelve months of twenty-nine or thirty days that each begin on the first day of a new moon. Leap months, rather than days, are added as needed.

# የዘመን ቀመር (Calendar System)

## The Ethiopian Calendar

If you live in Ethiopia, you're behind time…literally. Based on alternate calculations of the date of the announcement of Jesus Christ's birth, the Ethiopian calendar is seven years behind, with its new year corresponding to September 11th of the Gregorian calendar – or September 12th if it's a leap year. That puts right now at early 2012 in Ethiopian time.

# የዘመን ቀመር (Calendar System)

## The Hebrew or Jewish Calendar

Like the Chinese calendar, the Jewish calendar is lunar, with each month commencing with the new moon. The issue with strictly lunar calendars is that there are approximately 12.4 lunar months to each solar year, so a twelve-month lunar calendar is slightly too short, while a thirteen-month lunar calendar is slightly too long.

# የዘመን ቀመር (Calendar System)

## The Islamic, Muslim or Hijrī Calendar

The Islamic calendar is also lunar, but unlike the Hebrew or Chinese calendars, it does not use leap months or days to account for the difference in length of the solar year. Therefore, the named months do not remain in the same seasons. Instead, they slowly retrogress through the entire solar year, taking thirty-two and a half years to reoccur at the same seasonal time.

# የዘመን ቀመር (Calendar System)

## The Persian or Solar Hijiri Calendar

The Persian calendar has been called “one of the world’s most accurate calendar systems.” Like the Islamic calendar, it dates back to Muhammad’s Hegira in 622 CE, but it is otherwise quite different. It’s a solar calendar, rather than a lunar one, with the year beginning on midnight of the vernal equinox in Iran. There are twelve months, of which the first six have thirty-one days, the second five have thirty days, and the last month, Esfand, alternates between having twenty-nine days or thirty days in a leap year.

# ቀመረ ዘመን

የኢትዮጵያ ቀመረዘመን በውስጡ አራት ዐበይት ክፍሎችን አካቶ ይዟል።

1. መርሐ ዕውር
2. አቡሻኽር
3. ሐሳበ ፈለክ
4. ሐሳበ ነፋሳት

# ቀመረ ዘመን

መርሐ ዕውር  ቀመረ ድሜጥሮስን በመጠቀም ዕለታት ፤ ዘመናት ፤ አጽዋማት ፤ በዓላት የሚውሉበትን  ጊዜ በመጥቅዕ ፤ በአበቅቴ ፤ በጥንተዮን እና በሌሎችም አቅማራት እየቀመረ ያስረዳል።

# የግብራና መጻህፍት ዳሰሳ

- አቡሻኽር
- ባሕረ ሐሳብ
- ስነ ፈለክ

# ቀመረ ዘመን

- ከድሜጥሮስ አስቀድመው የነበሩ ሊቃውንት አፅዋማት በአላት እየተፋለሱባቸው ሲያዝኑ ሲተክዙ ይኖሩ ነበር
- ፆመ ኢየሱስን የጥምቀት ሳኒታ አስገብተው የካቲት22 ይጨርሳሉ
- በ22ት ሆሳዕና ፤ በ27ት ስቅለትን ፤በ29ኝ ትንሳኤን ያደርጉ ነበር

# ቀመረ ዘመን

- ትንሳኤም እንደዛሬው እሁድ ብቻ አይውልም ነበር። ሰኞ ፤ ማክሰኞ ፤ ረቡዕ ፤ ሃሙስ ፤ አርብ ፤ ቅዳሜ እንደተገኘ ይውል ነበር።
- አዝማናቱንም ሶስቱን ወርህ ከአንድ ጳጉሜ ለአንድ ወንጌላዊ ሶስቱን ወርህ ከአንድ ጳጉሜ ለአንድ ወንጌላዊ አድርገው አካፍለዋቸዋል።

# ቀመረ ዘመን

- አምስተኛይቱን ከነግህ እስከቀትር ለአንድ ወንጌላዊ ፤ ከቀትር እስከ ሰርክ ለአንድ ወንጌላዊ ፤ ከሰርክ እስከመንፈቀሌሊት ለአንድ ወንጌላዊ ፤ ከመንፈቀ ሌሊት እስከነግህ ለአንድ ወንጌላዊ ፤ አድርገው አካፍለዋቸዋል።
- ስድስተኛይቱን ለአራቱ ከዋክብት በኬክሮስ አካፍለዋቸው ይኖሩ ነበር።

# ቀመረ ዘመን

- ከዚህም በኋላ መልአኩ ተገልጾለት ድሜጥሮስ ዘወትር በተምኔት የሚፈጸም መስሎሃል ከሌሊቱ 23 ከመዓልቱ 7ት ሱባኤ ገብተህ እየው አለው።

# ቀመረ ዘመን

❖ የሌሊቱን አብዝቶ የቀኑን ስለምን አሳነሰ ቢሉ ቀን የታመመ ሲያይ ፤ የሞተ ሲያሥቀብር ፤ የተጣላ ሲያሥታርቅ ፤ ሲፈርድ ፤ ሲተች ይውል ነበርና የቀኑን አሳንሶ የሌሊቱን አበዛው ሌሊቱስ 24ት ነው እንጂ 23ት ነው ቢሉ ባንዲቷ ሰአት ጥቂት ጥቂት ያርፍባት እህል ይቀምስባት ነበር።

# ቀመረ ዘመን

- የሌሊቱ 7ት ጊዜ 23ት ሲባዙት 161 ይሆናል በ5ት30 ሲገድፉት 11ድ ይተርፋል ይህንን አበቅቴ በለው በዚህ ላይ ህጻጽ መዓልት እየጨመርክ ሌሊት አሳድር

- የቀኑን ሰባት ጊዜ ሰባት ቢደምሩት 49 ይሆናል በ30 ሲገድፉት 19 ይተርፋል ይህንን መጥቅዕ በለው መባጃ ሀመሩን ከአጽዋማትና ከበዓላት ተውሳክ ጋር እየጨመርክ አጽዋማትና በዓላትን ታወጣበታለህ ብሎታል

# ቀመረ ዘመን

- 11 አበቅቴ ፤ 19 መጥቅዕ ሲደምሩት 30 ይሆናል አበቅቴ ቢበዛ መጥቅእ ቢያንስ ከ30 አይወጡም አይወርዱም። መጥቅዕ ወአበቅቴ ኢየዐርጉ እምሰላሳ ወኢይወርዱ እምሰላሳ ወትረ ይከውኑ ሰላሳ እንዲል።

$$11 + 19 = 30$$

# ቀመረ ዘመን

- እርሱ ግን ፆመነነዌ ፡ ፆመኢየሱስ ፡ ፆመሃዋርያት ከሰኞ ፤ ርክበ ካህናት ፡ ምህላ ፆም ከረቡዕ ፤ ዕርገት ከሃሙስ ፤ ስቅለት ከአርብ ፤ ደብረዘይት ፡ ሆሳዕና ፡ ትንሳኤ ፡ ጰራቅሊጦስ ከ እሁድ እንዳይወጡ ወሰኗል።
- አዝማናቱንም 12ት ወርህ ከ5ጳጉሜ ለአንድ ወንጌላዊ ፤ 12ት ወርህ ከ5 ጳጉሜ ለአንድ ወንጌላዊ ስድስተኛይቱን ለሉቃስ ሰጥቶታል ስለምን ቢሉ ስም ስላነሰው አንድም በሱ ዘመን ስለሆነች።

# ቀመረ ዘመን

ቋሚ የማይለወጡ አቅማራት

- ❖ ጥንተ አበቅቴ = 11
- ❖ ጥንተ መጥቅዕ = 19
- ❖ ዓመተ ፍዳ (ዓመተ ኲነኔ) = 5500

# ቀመረ ዘመን

ለዘመን መስፈሪያ መቁጠሪያ የሚሆኑ 7 አዕዋዳት አሉት።

ምንና ምን ቢሉ

- ዐውደዕለት ፤
- ዐውደወርህ ፤
- ዐውደአመት ፤
- ዐውደፀሀይ ፤

# ቀመረ ዘመን

- ዐውደጨረቃ ፤
- ዐውደአበቅቴ ፤
- ዐውደማህተም ፤
- ዐውደቀመር ናቸው።

# ቀመረ ዘመን

- ዐውደዕለት ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ ከእሁድ እስከ ቅዳሜ ያሉት ሰባቱ ዕለታት ናቸው እሊህ ሲደርሱ ተመልሶ አንድ ይላል እንጂ ስምንት ዘጠኝ አይልም። እሊህም አውራህን ለማስገኘት ሲመላለሱ ይኖራሉ።

# ቀመረ ዘመን

- ዐውደወርህ ማለት ምን ማለት ቢሉ በጸሀይ ዘወትር 30 ፤ በጨረቃ አንድ ጊዜ 29ኝ አንድ ጊዜ 30 ዕለታት ናቸው እሊህ ሲደርሱ ተመልሶ 1 ይላል እንጂ 31ድ 32ት አይልም። እሊህም አመታትን ለማስገኘት ሲመላለሱ ይኖራሉ።

# ቀመረ ዘመን

- ዐውደአመት ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ 365 በዘመነ ሉቃስ 366 እለታት ናቸው እሊህ ሲደርሱ ተመልሶ አንድ ይላል እንጂ 367ት368ት አይልም እሊህ ሲመላለሱ ይኖራሉ።

# ቀመረ ዘመን

- ዐውደጨረቃ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ 354 እለታት ናቸው። እሊህ ሲደርሱ ተመልሶ አንድ ይሳል እንጂ 355ት 356ት አይልም እሊህ ሲመላለሱ ይኖራሉ።

- እሊህ አራቱ በእለት ሶስቱ በአመት ይቆጠራሉ።

# ቀመረ ዘመን

- ዐውደአበቅቴ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ 19ኝ 19ኝ ዘመን የሚቀመርበት ንዑስቀመር ይባላል። በዚህም ፀሀይና ጨረቃ መንገዳቸውን ዓውደ አመታቸውን እየፈጸሙ በተፈጠሩበት ኆኅት ተራክቦ ያደርጉበታል

# ቀመረ ዘመን

- ዐውደማህተም ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ 76ት 76ት ዘመን የሚቀመርበት ማዕከላዊ ቀመር ይባላል። በዚህም አበቅቴና ወንጌላዊ ይገናኙበታል አበቅቴው 18ት ወንጌላዊው ዮሐንስ ነው ፤ አበቅቴው ለአበቅቴ ፍጻሜ እንደሆነ ወንጌላዊውም ለወንጌላውያን ፍጻሜ ነውና።

# ቀመረ ዘመን

- ዐውደቀመር ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ 532ት 532ት ዘመን የሚቀመርበት ዐቢይ ቀመር ይባላል። በዚህም አበቅቴ ዕለት ወንጌላዊ ይገናኙበታል አበቅቴው 18 ፤ ዕለቱ ዕለተ እሁድ ፤ ወንጌላዊው ዮሐንስ ነው።

# ቀመረ ዘመን

- ዓውደ ጸሀይ የተባለ 28 ዘመን ነው በዚህም ዕለት ፤ ወንጌላዊ ይገናኙበታል። እለቱ ረቡዕ ወንጌላዊው ማቴዎስ ነው።

# ቀመረ ዘመን

- ዐቢይ ቀመር መደቡ አስራ አራትም አስራ አምስትም ይሆናል የሚደርሰው ቁጥሩም 532ት 532ት ነው ፤
- ማዕከላዊ ቀመር መደቡ ስድስትም ሰባትም ይሆናል የሚደርሰውም ቁጥሩም 76ት 76ት ነው ፤
- ንዑስ ቀመር መደቡ ሶስትም አራትም ይሆናል የሚደርሰው ቁጥሩም 19ኝ 19ኝ ነው።

# ቀመረ ዘመን

የአመቱን ቀመር ለመስራት የሚያስፈልጉን ቀመሮች

- መደብ
- ወንበር
- አበቅቴ
- ህጸጽ
- መጥቅዕ

# ቀመረ ዘመን

- የእለታት ተውሳክ
- መባጃ ሐመር
- የአጽዋማት ተውሳክ

# ቀመረ ዘመን

## መደብ (Step 1)

አመተኩነኔ + አመተምህረት = አመተአለም

5500 + 2013 = 7513

# ቀመረ ዘመን

## መደብ (Step 2)

ዐበይ ቀመር = 532

የዐበይ ቀመር መደብ = 14

ንዑስ ቀመር = 19

የንዑስ ቀመር መደብ = 3

# ቀመረ ዘመን

## መደብ (Step 3)

የዓቢይ ቀመር ብዜት = የዐቢይ ቀመር ቁጥር x የዐቢይ ቀመር መደብ

የዓቢይ ቀመር ብዜት = 14 x 532 = 7448

የዓቢይ ቀመር ትርፍ = አመተ አለም - የዓቢይ ቀመር ብዜት

የዓቢይ ቀመር ትርፍ = 7513 – 7448 = 65

# ቀመረ ዘመን

## መደብ (Step 4)

መደብ = የዓቢይ ቀመር ትርፍ % ንዑስ ቀመር

መደብ = 65 % 19 = 8

# ቀመረ ዘመን

## ወንበር (Step 1)

ወንበር = መደብ – 1

ወንበር = 8 – 1 = 7

**አሐደ አዕትት ለዘመን**

# ቀመረ ዘመን

የአመቱ አበቅቴ = ጥንተአበቅቴ x ወንበር

የአመቱ መጥቅዕ = ጥንተመጥቅዕ x ወንበር

የአመቱ አበቅቴ = 11 x 7 = 77

የአመቱ መጥቅዕ = 19 x 7 = 133

# ቀመረ ዘመን

ከ30 በላይ ከሆነ ፤ በ30 ይገደፋል (Find the reminder)

የአመቱ አበቅቴ = 77 % 30 = 17

የአመቱ መጥቅዕ = 133 % 30 = 13

# ቀመረ ዘመን

## ህጸጸ አውራኅ

- በዘመነ ማቴዎስ መስከረም መዐልቱ 30 ሌሊቱ 30 በአንድ ላይ 60 ይሆናል በ 4 ት በ 4 ት ሱባኤ ሲገድፉት 4 ት ይተርፋል። የጥቅምት መዐልቱ 30 ሌሊቱ 30 በአንድ ላይ ስልሳ ይሆናል በ 4 ት በ 4 ት ሱባኤ ሲገድፉት 4 ት ይተርፋል።

- የመጀመሪውና የአሁኑ 4 ት ሲደመሩ ስምንት ይተርፋል። በአንድ ሱባኤ ሲገድፉት አንድ ይተርፋል። 1 ህፅፅ ከዚህ ተገኘ።

- ህዳርና ታህሳስ ፧ ጥርና የካቲት ፧ መጋቢትና ሚያዝያ ፧ ግንቦትና ሰኔ ፧ ሀምሌና ነሃሴ እንዲህ እያልክ አውጣ። በአመቱ ውሥጥ ስድስት ህፀፅ ይገኛል።

# ቀመረ ዘመን

## ህጸጸ አውራኅ

የመስከረም መዓልት = 30

የመስከረም ሌሊት = 30

ዕለታት = 7

የመስከረም ትርፍ = የመስከረም መዓልት + የመስከረም ሌሊት

የመስከረም ትርፍ = 30 + 30 = 60

*የመስከረም ትርፍ = 60 % 7 = 4*

# ቀመረ ዘመን

## ህጸጸ አውራኅ

የጥቅምት መዓልት = 30

የጥቅምት ሌሊት = 30

ዕለታት = 7

የጥቅምት ትርፍ = የመስከረም መዓልት + የመስከረም ሌሊት

የጥቅምት ትርፍ = 30 + 30

***የጥቅምት ትርፍ = 60 % 7 = 4***

# ቀመረ ዘመን

## ህጸጸ አውራኅ

የጥቅምት መዓልት = 30

የጥቅምት ሌሊት = 30

ዕለታት = 7

የጥቅምት ትርፍ = የመስከረም መዓልት + የመስከረም ሌሊት

የጥቅምት ትርፍ = 30 + 30

***የጥቅምት ትርፍ = 60 % 7 = 4***

# ቀመረ ዘመን

## ህጸጸ አውራኅ

ህጸጸ መስከረም ወጥቅምት = የመስከረም ትርፍ + የጥቅምት ትርፍ

ህጸጸ መስከረም ወጥቅምት = 4 + 4

*ህጸጸ መስከረም ወጥቅምት = 8 % 7 = 1*

# ቀመረ ዘመን

## ሠርቀ ሌሊት

ሠርቀ ሌሊት = ሠርቀ መዓልት + ህጸጽ + አበቅቴ

የመስከረም 1 ሠርቀሌሊት = የመስከረም 1 ሠርቀ መዓልት + የመስከረም ህጸጽ + አበቅቴ

የመስከረም 1 ሠርቀ ሌሊት = 1 + 1 + 17

*የመስከረም 1 ሠርቀ ሌሊት = 19*

# ቀመረ ዘመን

**ሠርቀ ወርህ**

**ሠርቀ ወርህ (የጨረቃ መውጫ) = ሠርቀ ሌሊት + 4**

**የመስከረም 1 ሠርቀ ወርህ = የመስከረም 1 ሠርቀ ሌሊት + 4**

***የመስከረም 1 ሠርቀ ወርህ = 19 + 4 = 23***

# ቀመረ ዘመን

- ሠርቀ መዓልት የሚባለው የብርሃናማው ቀን ቁጥር ነው። ለምሳሌ የመስከረም 1 ሠርቀ መዓልት 1 ነው። የመስከረም 2 ሠርቀ መዓልት 2 ነው።

- ሠርቀ ዕለት የሚባሉ ሰባቱ እለታት ናቸው እሊህም አሚር ፤ ሰኑይ ፤ ሠሉስ ፤ ረቡዕ ፤ ሐሙስ ፤ ሰዱስ ፤ ሰቡዕ ናቸው።

# ቀመረ ዘመን

## በዓለ መጥቅዕ

- መጥቅዕ 14 ትን አይነካም ከ 14 ት በላይ የሆነ እንደሆነ ከ 15 ት እስከ 29 ይወለዳል። መጥቅዕ በመስከረም ይወድቃል። ፆመነነዌ በጥር ይሆናል።

- ከ 14 ት በታች የሆነ እንደሆነ ከ 1 ድ እስከ 13 ይወለዳል መጥቅዕ በጥቅምት ይወድቃል። ፆመነነዌ በየካቲት ትሆናለች።

# ቀመረ ዘመን

## በዓለ መጥቅዕ

መጥቅዕ $\neq$ 14

if (መጥቅዕ > 14)

በዓለ መጥቅዕ = መስከረም

ጾመ ነነዌ = ጥር

if (መጥቅዕ < 14)

በዓለ መጥቅዕ = ጥቅምት

ጾመ ነነዌ = የካቲት

# ቀመረ ዘመን

## በዓለ መጥቅዕ

የዕለታት ተውሳክ በቅዳሜ ተጀምሮ በአርብ ያልቃል።

- ❖ የቅዳሜ 8
- ❖ የእሁድ 7
- ❖ የሰኞ 6
- ❖ የማክሰኞ 5
- ❖ የረቡዕ 4
- ❖ የሃሙስ 3
- ❖ የአርብ 2 ነው።

# ቀመረ ዘመን

## በዓለ መጥቅዕ

የ 2013 መጥቅዕ = 13

13 < 14 = True

በዓለ መጥቅዕ = ጥቅምት

# ቀመረ ዘመን

## በዓለ መጥቅዕ

ስለዚህ የጥቅምት 13ትን እለት እንፈልጋለን። መስከረም አርብ ይብታል ፤ ጥቅምት እሁድ ይብታል። ከእሁድ እስከ እሁድ 8 ፤ ከእሁድ እስከ እሁድ 15 ፤ ቅዳሜ 14 ፤**አርብ 13** ይሆናል።

የአርብ ተውሳክ 2 ት ነው። 2 ትና 13 ትን ቢገጥሟቸው 15 ት ይሆናል። ***15 ት መባጃ ሀመር በዘመነ ማቴዎስ ተገኘ***።

# ቀመረ ዘመን

## በዓለ መጥቅዕ

መባጃ ሐመር = የበዓለ መጥቅዕ እለት ተውሳክ + መጥቅዕ

መባጃ ሐመር = 2 + 13

መባጃ ሐመር = 15

# ቀመረ ዘመን

## አጽዋማት

መጥቅዕ ከአስራአራት በታች በመሆኑ ያመነነዌ በየካቲት ትወድቃለች ። የካቲት ሰኞ ይብታል።

ከሰኞ እስከ ሰኞ 1 ድ ፤ ከሰኞ እስከ ሰኞ 8 ፤ ከሰኞ እስከ ሰኞ 15 ይሆናል። የካቲት 15 ት ሰኞ ያመነነዌ ትሆናለች፡ ፡

# ቀመረ ዘመን

## አጽዋማት

### የአፅዋማት ተውሳክ

- የፆመ ኢየሱስ 14
- የደብረ ዘይት 11
- የሆሳዕና 2
- የስቅለት 7
- የትንሳኤ 9
- የርክበ ካህናት 3
- የዕርገት 18
- የጰራቅሊጦስ 28
- የፆመ ሐዋርያት 29
- የፆመ ድህነት 1 ነው።

# ቀመረ ዘመን

## አጽዋማት

ጾም/ በዓል = የጾም / የበዓል ተውሳክ + መባጃ ሐመር

ጾመ ኢየሱስ = 14 + 15 = 29

የፆመኢየሱስ ተውሳክ 14 ት ነው። 14 ትና 15 ትን ቢገጥሟቸው 29 ኝ ይሆናል። የካቲት ሰኞ ይብታል። ከሰኞ እስከ ሰኞ 1 ድ ፤ ከሰኞ እስከ ሰኞ 8 ፤ ከሰኞ እስከ ሰኞ 15 ፤ ከሰኞ እስከ ሰኞ 22 ፤ ከሰኞ እስከ ሰኞ 29 ይሆናል። የካቲት 29 ኝ ሰኞ ፆመኢየሱስ ይሆናል።

# ቀመረ ዘመን

## አጽዋማት

ጾም/ በዓል = የጾም / የበዓል ተውሳክ + መባጃ ሐመር

ደብረ ዘይት = 11 + 15 = 26

የደብረዘይት ተውሳክ 11 ድ ነው። 11 ድና 15 ትን ቢገጥሟቸው 26 ት ይሆናል። መጋቢት ረቡዕ ይብታል ከረቡዕ እስከ ረቡዕ 1 ፤ ከረቡዕ እስከ ረቡዕ 8 ፤ ከረቡዕ እስከ ረቡዕ 15 ፤ ከረቡዕ እስከ ረቡዕ 22 ፤ ሐሙስ 23 ፤ አርብ 24 ፤ ቅዳሜ 25 ፤ እሁድ 26 ይሆናል። መጋቢት 26 ት እሁድ ደብረዘይት ይሆናል።

# ቀመረ ዘመን

## አጽዋማት

ጾም/ በዓል = የጾም / የበዓል ተውሳክ + መባጃ ሐመር

ሆሳዕና = 2 + 15 = 17

የሆሳዕና ተውሳክ 2 ት 15 ትን ቢገጥሟቸው 17 ይሆናል። ሚያዝያ አርብ ይብታል ከአርብ እስከ አርብ 1 ፤ ከአርብ እስከ አርብ 8 ፤ ከአርብ እስከ አርብ 15ይሆናል። አርብ 15 ፤ ቅዳሜ 16 ፤ እሁድ 17 ይሆናል። ሚያዝያ 17 ት እሁድ ሆሣእና ይሆናል።

# ቀመረ ዘመን

## አጽዋማት

ጾም/ በዓል = የጾም / የበዓል ተውሳክ + መባጃ ሐመር

ስቅለት = 7 + 15 = 22

የስቅለት ተውሳክ 7 ት 15 ትን ቢገጥሟቸው 22 ት ይሆናል። ሚያዝያ አርብ ይብታል። ከአርብ እስከ አርብ 1 ፤ ከአርብ እስከ አርብ 8 ፤ ከአርብ እስከ አርብ 15 ይሆናል ፤ ከአርብ እስከ አርብ 22 ይሆናል። ሚያዝያ 22 አርብ ስቅለት ይሆናል።

# ቀመረ ዘመን

## አጽዋማት

ጾም/ በዓል = የጾም / የበዓል ተውሳክ + መባጃ ሐመር

ትንሳኤ = 9 + 15 = 24

የትንሳኤ ተውሳክ 9 ኝና 15 ትን ቢገጥሟቸው 24 ት ይሆናል። ሚያዝያ አርብ ይብታል። ከአርብ እስከ አርብ 1 ፤ ከአርብ እስከ አርብ 8 ፤ ከአርብ እስከ አርብ 15 ይሆናል ፤ ከአርብ እስከ አርብ 22 ይሆናል ፤ ቅዳሜ 23 ት ፤ እሁድ 24 ት ይሆናል። ሚያዝያ 24 ት እሁድ ትንሳኤ ይሆናል።

# ቀመረ ዘመን

## Assignment

የርክበ ካሕናት ፤ የዕርገት ፤ የጰራቅሊጦስ ፤ የጾመ ሐዋርያት እና የጾመ ድህነትን የሚውሉበትን ወር ፤ ሠርቀ መዓልት ፤ ሠርቀ ሌሊት ፤ ሠርቀ ወርህ ፤ ሠርቀ ዕለት አውጡ።

# በረከተ ሊቃውንት አበዊነ ይህድር በላዕለ ኵልነ

Contact: ye46427@gmail.com | +251921625794